የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ
*The Holy synod of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church*

No 2038/2014
Date 15/16/2014

**ከግንቦት ፮- ፰, ፪ሺ፮ ዓ.ም (MAY 14-16,2014) በኦክላንድ መካነ ሰላም መድኃኔዓለም ካቴድራል በተካሄደው ሷ፱ነኛው ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠ መግለጫ**

«ሰላምየ አኅድግ ለክሙ ወሰላመ አቡየ እሁበክሙ። ሰላሜን እተውላችኋለሁ ፤ የአባቴን ሰላም እሰጣችኋለሁ።» ዮሐንስ 14 ፥፳፯

## መግቢያ

በነቢያት ትንቢት በሐዋርያት ትምህርት ጸንታ የኖረችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ፣ የቋንቋ ፣ የባህልና የትውፊት ምንጭ ሆና የኖረች ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን ናት። ለሕዝቧ የሃይማኖቱ እና የባህል ምንጭና ማዕከል ሆና የኖረችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሰፊ በሆነው ታሪኳ ዛሬ ኢትዮጵያ በመላው ዓለም ለምትታወቅበትና ለምትኮራበት ማንነት መሠረት በመሆኑዋ ኢትዮጵያን የሚወዱና የኢትዮጵያን ታሪክ በጥልቀት የሚያጠኑ ሁሉ ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ጥልቅ አክብሮት ሲያሳዩ እናያለን።

ይህ ሲባል ግን ቤተ ክርስቲያን ረጅም በሆነው ታሪካዊ ጉዞዋ ፈተናዎች ሳያጋጥሙአት ቀርተው አይደለም። ከዮዲት ጉዲት እስከ ግራኝ ሰይፍና የፋሽሽት ጣልያን ግፍ ቤተ ክርስቲያናችን ብዙ መከራዎችን አሳልፋለች ፤ አሁንም በዘመናችን ውስብስብ የሆኑና ሕልውናዋን የሚፈታተኑ ፈተናዎች አጋጥመዋታል። ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ፈርሷል ፣ ሕጋዊው ፓትርያርክ ተሰደዋል። በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ለአገዛዙ እንዲያመቸው የቤተ ክርስቲያኒቱን ውስጣዊ ነጻነት በማፈን የራሱን የፖለቲካ መሪዎችን ፣ የሃይማኖት መሪዎች አድርጎ ከማስቀመጡም በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያኒቱን ዶግማና ቀኖና እኛ ጽፈን እንሰጣችሁ እስከማለት ደርሶአል። ሆኖም ግን እግዚአብሔር አምላክ ኃይልና ረድኤት ሆኖአት እነዚህን ፈታኝ ዘመናት አልፋ እስከ አሁን ደርሳለች። ወደፊትም ራሷና መሠረቷ የሆነው ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም እስከሚመጣ የትውልድ ብርሃን ሆና ትቀጥላለች።

በዘመናችን ይህችን ቤተ ክርስቲያን ለመምራት ከመንፈስ ቅዱስ አደራ የተረከበው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው የሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ሷ፱ኛ መደበኛ ጉባኤን ከግንቦት ፮-፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ/ም በመካነ ሰላም መድኃኔ ዓለም ካቴድራል አስተናጋጅነት በኦክላንድ ካሊፎርንያ አካሂዶአል። ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በመደበኛ ስብሰባው ላይ በቤተ ክርስቲያናችን ሃይማኖታዊ ፣ ሀገራዊና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በጥልቀት ተወያቶ የሚከተሉትን ውሳኔዎች አስተላልፎአል።

## 1. የሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስን አንድነትና ሰላም በተመለከተ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬስ ፓርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት የሚመራው ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ቤተ ክርስቲያንን በስደት በመላው ዓለም ተበትኖ ላለው ሕዝብ የሰላም የፍትህና የመጽናናት ምንጭ ሆኖ ቆይቶአል። እግዚአብሔር በስደት ያለነውን ስደታችንን እንኳን የባረከልን አብያተ ክርስቲያናትም የሰፋፉት ሕዝበ ክርስቲያንም በሃይማኖት የታነጹት ደግሞ በፍቅርና በሰላም ሆነን ሕዝባችንን በማገልገላችን እንደሆነ እናምናለን። በመሆኑም በዚህ



*4127 Redwood Rd. Oakland CA 94619 Tel: (510) 530 3681*

በ፴፱ኛው መደበኛ የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ላይ ለፍቅርና ለእርቅ ቅድሚያ በመስጠት ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት እስከ ምእመናን ድረስ የጉባኤው ተሳታፊዎች ይቅር በመባባል ጠላት ዲያብሎስ በመካከላችን ሊገነባ የሞከረውን የመለያየት ወጥመድ አስወግደናል። የጉባኤው ተሳታፊዎችም ሰላምን ፍቅርን በማጽናት በአንድ ልብ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ቃል ገብተዋል። አንድ ሥራ ሲሠራ የሐሳብ ልዩነት ሊፈጠር ይችላል። ቁልፉ ግን በቅንነትና በመደማመጥ ማስተካከል እንዲሁም በፍቅር ሆኖ ለቀኖና ቤተ ክርስቲያንና ለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ተገዢዎች መሆን ነው። በልዩ ልዩ የሥራ ሂደት ምክንያት ተፈጥሮ የነበረውን ቅሬታ ሙሉ መፍትሄ በመስጠት የራቁትን በማቅረብ በሰላምና በፍቅር ለመስራት በአንድነት ተነሥተናል። ያለውም የሰላም ኮሚቴ ተጠናክሮ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ያለውን ችግር መፍትሔ እንዲፈልግ ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኖአል። በመላው ዓለም የሚገኙ በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ሥር የሚገኙ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻችንንም ይህን የእርቅና የሰላም መንፈስ ተከትላችሁ እንድትጓዙ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ሲያቀርብ ሲኖዶሱ « ሰላሜን እሰጣችኋለሁ» በሚል ርእስ የሰላም ጉባኤ በመላው ዓለም በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት የስብከተ ወንጌል ሐዋርያዊ ሥምሪት በአስቸኳይ እንዲደረግ ተወስኖዋል።

## 2. በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ስም የሚወጡ መግለጫዎችንና ጽሑፎችን በተመለከተ

በሕጋዊው ቅዱስ ፓትርያርክ የሚመራው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ መግለጫዎቹን የሚያወጣው በሥሩ ባቋቋመው መምሪያ እና አርማዎቹን በያዙ ደብዳቤዎች ነው። መግለጫዎች የሚወጡትም በምልዓተ ጉባኤው ውይይት ተደርጎባቸውና ጸድቀው ነው። ይህ ሳይሆን ሲኖዶሱን በማይወክል መንገድና የሲኖዶሱን አርማ ሳይይዙ ሲኖዶሱ ያልወሰነውን እንደወሰነ ፣ ያላጸደቀውን እንዳጸደቅ ተደርገው በድህረ ገጾች ወይም በዌብ ሳይቶችና በመገናኛ ብዙኃን የሚወጡት መግለጫዎችና ጽሑፎች የሲኖዶሱን ሕልውና በእጅጉ እየተፈታተኑት ይገኛል። በመሆኑም የመገናኛ ብዙኃን ኃላፊነትን በተመላ መንገድ የመረጃ ምንጮችን በማጥናት ሲኖዶሱን የሚመለከቱ መግለጫዎችንና ጽሑፎችን ከሲኖዶሱ ሲላክላቸው ብቻ እንዲያወጡ ጥሪያችንን እናቀርባለን። ሕዝበ ክርስቲያኑ በሕገወጥ መግለጫዎችና ጽሑፎችም እንዳይናወጡና እንዳይቀበሉአቸው እናሳስባለን። ያለ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ የሚወጡትን ሕገወጥ መግለጫዎችና ጽሑፎች በተመለከተ ቅዱስ ሲኖዶሱ እየተከታተለ በመገናኛ ብዙኃን አስፈላጊውን መልስ እንደሚሰጥም በጥብቅ ያስታውቃል። የመገናኛ ብዙኃንም ሲኖዶሱን በሚመለከት ማናቸውንም መረጃዎች ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ማግኘት ስለሚችሉ ከቅዱስ ሲኖዶስ የሕዝብ ግንኙነት መምሪያ ጋር አስፈላጊውን መስመር እንዲዘረጉም መንፈሳዊ ጥሪ እናቀርባለን።

## 3. የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት በተመለከተ

የሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ መንበረ ፓትርያርክ በተጠናከረ መንገድ እንዲቋቋም ፣ እንደዚሁም ለቅዱስ ፓትርያርኩ መኖሪያ የሚሆን ቦታ የቤተ ክርስቲያንን ክብር በጠበቀ መንገድ እንዲዘጋጅ መወሰኑ ይታወሳል። ስለሆነም በመላው ዓለም በቅዱስ ሲኖዶስ ሥር የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም በጎ አድራጊዎች ምዕመናን ባደረጉት ከፍተኛ ርብርብ የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት ሕንፃ ባለቤት ሆነናል። ቅዱስ አባታችንም በአዲሱ መንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት ሆነው በመላው ዓለም ያሉ ልጆቻቸውን እየመሩ ይገኛሉ። አሁንም መንበረ ፓትርያርኩን በማጠናከር ረገድ በመላው ዓለም ያሉ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች አቅማቸው በፈቀደ መንገድ ለመንበረ ፓትርያሪክ ጽ/ቤት አስፈላጊውን እርዳታ በማድረግ እንዲተባበሩ ቅዱስ ሲኖዶስ ያሳስባል። ይህ ሁሉ መንፈሳዊ ዕድገት ሊታይ የቻለውም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ለልጆቻቸው በሚሰጡት ፍቅርና ሰላምን የተመላ መንፈሳዊ አመራር እንዲሁም በቅዱስ ሲኖዶስ ጥንካሬ መሆኑ ግልጥ ነው። በመሆኑም እግዚአብሔር አምላክ ለብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ረጅም እድሜና ጤናን እንዲሰጥልን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትጸልያለች።

## 4. በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ አብሮ ለመሥራት በመምጣት ላይ ስላሉ አብያተ ክርስቲያናት

ቅዱስ ሲኖዶስ ቀኖና ፈረሰ ሕግ ተጣሰ በማለት ከተሰደደበት ጊዜ ጀምሮ የቅዱስ ሲኖዶስን ዓላማ ዓላማቸው ያደረጉ አብያተ ክርስቲያናት በየጊዜው ከቅዱስ ሲኖዶስ ጋር በመሆን

በአንድነት በመጓዝ ላይ ናቸው። በአሁኑ ወቅትም በአውሮፓና በአሜሪካ በገለልተኝነት የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ለመመራት በጠየቁት መሠረት ቅዱስ ሲኖዶስ እጁን ዘርግቶ ተቀብሎአቸዋል። በመላው ዓለም የሚገኙ አዲስ የሚቋቋሙና በገለልተኝነት ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ለቤተ ክርስቲያናችን ድምጽ በመሆን በአንድነት ቀናና ቤተ ክርስቲያንን ለማስጠበቅና እምነታችንን ለማጽናት እንድንሠራ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል።

## <u>5. የጠቅላይ ቤተ ክህነትን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ</u>

የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ከተዋቀረበት ጊዜ ጀምሮ በጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ በኩል የተሠሩ ሥራዎችን ፣ ያጋጠሙ ችግሮችን እንዲሁም የወደፊት የዕድገት አቅጣጫዎችን ያጠቃለለ ሪፖርት ቀርቦ ጉባኤው በሰፊው ተወያይቶአል። በመሆኑም የጠቅላይ ቤተ ክህነት በሚገባ እንዲደራጅ አስፈላጊው እገዛ እንዲደረግለት ፥ በረቂቅ ደረጃ ያለው አጠቃላይ ሕገ ደንብ ተጠንቶ እንዲጸድቅ ፥ የቤተ ክርስቲያኒቱን ዘርፈ ብዙ የሆኑ አገልግሎቶች በተቀናጀ መልኩ ማከናወን ይቻል ዘንድ የጠቅላይ ቤተ ክህነቱ መምሪያዎች በሚገባ ተጠናክረው አገልግሎታቸውን እንዲቀጥሉ ጉባኤው ወስኖአል።

## <u>6. የካህናት ሥልጠናና የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ በተመለከተ</u>

የሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ዓላማ ሕዝበ ክርስቲያኑን በትምህርተ ሃይማኖት ማጽናት እና ተተኪ ትውልድ ማፍራት ነው። የነገይቱን ቤተ ክርስቲያን ተረካቢዎች ለማፍራት ማዕከላዊነት ያለው ሥርዓተ ትምህርት መቅረጽ እንደሚገባ ጉባኤው አምኖበታል። ይህን የቤተ ክርስቲያንን ሰፊ የሆነ አገልግሎት ማከናወን የሚቻለው የምእመናንን የእውቀት ደረጃ ያገናዘበ ዕውቀት ያላቸው ካህናትን ማሰልጠንና ስልጠናውም ቋንቋን ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂንና የየአገሩን ባህል የሚያስተዋውቅ መሆን እንዳለበት በማሳሰብ የካህናት የሥልጠና ማዕከል እንዲቋቋም እንዲሁም ለወጣቶች እና ለሕፃናት የሚሆን ሥርዓተ ትምህርት በአስቸኳይ ተቀርጾ እንዲቀርብ ወስኖአል።

## <u>7. አህጉረ ስብከቶችን ፣ የሰበካ ጉባኤያትን ማደራጀትና የኤጲስ ቆጶሳትን ሹመት በተመለከተ</u>

በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ሥር ያሉ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የሰበካ ጉባኤና የቦርድ ሊቃነ መናብርት በአንድነት ተሰብስበው ለቤተ ክርስቲያን መስፋፋት ለምእመናን አንድነትና ሰላም መመካከር እንዳለባቸው ጉባኤው አምኖበታል። በመሆኑም በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ሥር የሚደራጀ የሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ በሚገባ ተዋቅሮና የመምሪያ ኃላፊ ተመድቦለት በቅዱስ ሲኖዶስ ሥር የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን ተቀራርበው በአንድነት ሲኖዶሱን በገንዘብ ፣ በሐሳብና በማናቸውም መልኩ የሚደግፉበትን መንገድ እንዲያስተባብር ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኖአል። እንደዚሁም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ ያለውን የሲኖዶሱን አገልግሎት ከግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መንገድ ሀገረ ስብከቶች እንዲዋቀሩ እና አዳዲስ ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙ ጉባኤው ወስኖአል።

## <u>8. የሰው ልጅ መብቶችን በተመለከተ</u>

ቅዱስ ሲኖዶስ ይህን መደበኛ ጉባኤውን በሚያካሂድበት ወቅት ስለ ዓለም ሰላም ጸሎት አድርጎአል። በተለይም አገራችን ኢትዮጵያ በምትገኝበት በአፍሪካ አህጉር በሚገኙት በደቡብ ሱዳን ፣ በመካከለኛው አፍሪካና በናይጄሪያ የሚከናወነው የሕዝቦችን ግጭት በታላቅ ሐዘን አስቦአል። የአፍሪካ ልጆች ከረሃብ ከእርስ በእርስ ግጭት ነፃ ወጥተው አህጉሪቱ ያላትን በረከት በሰላምና በፍቅር መጠቀም ሲገባ ጥቂት ሰዎች እያስተባበሩት ያለው የጎሣና የዘር ዕልቂት እጅግ አሳዝኖናል። በተለይም ደግሞ ሕፃናትን ማፈንና ጾታዊ ጥቃትን እንደመሣሪያ በማድረግ በናይጄሪያና በኮንጎ እየተከናወነ ያለውን በሴቶችና በሕፃናት ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍ ለማስቆም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባላት አገራትና በመላው ዓለም ያሉ የሃይማኖትና የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች በአስቸኳይ ርብርብ እንዲያደርጉ ጥሪውን ያቀርባል።

## 9. አብሮ በፍቅርና በሰላም ስለመኖር

አገራችን ኢትዮጵያ በአንድነትዋ ጸንታ የኖረችው ሕዝባቿ በመከባበር ዘር ፣ ጎሣና ሃይማኖት ሳይለያቸው በፍቅርና በሰላም ጸንተው በመኖራቸው ነው። ይህ የሕዝባችን አንድነት ደግሞ የአገራችን ታላቅ ሀብት ነው። ኢትዮጵያ የሰማዕታት ደም ያልፈሰሰባትና ሐዋርያት ያልተገደሉባት የሰላም አገር እንዳልሆነች ሁሉ ዛሬ የልጆችዋ ደም በከንቱ የሚፈስባት ምድር መሆኑዋ ግልጥ ነው። የሕዝባችንን አንድነት ለማናጋት በዘር እና በጎሣ ላይ የተመሠረተ ግጭት ለመፍጠር ሰሞኑን በወጣቶች ላይ የደረሰው የሞትና የአካል መጉደል አደጋ ቅዱስ ሲኖዶስን በእጅጉ አሳዝኖታል። ይህ በሥልጣን ላይ ባለው መንግሥት አማካይነት ያለፍትህና ያለፍርድ የሚደረግ ግድያ ድብደባ በትውልድ መካከል በቀልንና ጥላቻን ለማስረጽ ፣ ሕዝብ ከሕዝብ ጋር እንዳይተማመን የሚያደርግም ነው። በመሆኑም በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት አገርን ለመጠበቅ የተሰጠውን አፈሙዝ ወደ አገሪቱ ልጆች በማዞር ያለፍትሀ የሚያደርገውን ግድያ ቅዱስ ሲኖዶስ አጥብቆ ያወግዛል። በደረሰባቸው ድብደባ ሕይወታቸውን ላጡ ወገኖቻችን እግዚአብሔር አምላክ እረፍተ መንግሥተ ሰማያትን እንዲሰጣቸው እንዲሁም የአካል ጉዳትና የንብረት ውድመት የደረሰባቸውንም እግዚአብሔር ፍጹም ፈውሱንና መጽናናትን እንዲሰጥልን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትጸልያለች። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የልጆቹዋ የአንድነት ምልክት እንደመሆንዋ መጠን የእርስዋን ድምጽ የሚሰሙ ልጆቿና ሕዝቦቿ መካከል አንድነትን ፍቅርን በሚያመጡ ነገሮች ላይ ጸንተው እንዲመሩ በአገርም ውስጥ ይሁን በውጭው ዓለም የሚገኙ የፖለቲካ መሪዎች ሕዝብን ከሚለያይና ከሚከፋፍል ሥራና ድርጊት እንዲታቀቡ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል።

## 10. የቤተ ክርስቲያንን አንድነትንና ሰላም በተመለከት

ሕጋዊው ቅዱስ ፓትርያርክ ከመንበረ ክብራቸው ከተሰደዱበት ጊዜ ጀምሮ በአገር ቤት ባሉት አባቶችና በስደት ባለው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ መካከል የተፈጠረው ልዩነት በመላው ዓለም ያሉ የቤተ ክርስቲያን ልጆችን በከባድ ሐዘን ላይ ጥልአል። ይህን የቤተ ክርስቲያን ልዩነት ለመፍታት ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የሰላም እና የእርቅ ጥረቱን ሲያደርግ ቆይቶአል። አሁንም በቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል ያለው ልዩነት እየጠቀመ ያለው የቤተ ክርስቲያንን ጠላቶች ስለሆነ ቅዱስ ሲኖዶስ የእርቅ በሩን ክፍት አድርጎ ይጠባበቃል። የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያንም ሃይማኖቱን እምነቱን ታሪኩን እንዲጠብቅና ታሪኩን በማፍለስ እምነቱን በማዳከም ቤተ ክርስቲያኒቱ በአገራችን ያላትን ማዕከላዊ ሚና በማንኳሰስ የሚደረገውን ስውር ሥራ ነቅቶ እንዲጠብቅና በቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች መካከልም ሰላም እንዲሰፍን በጸሎት እንዲበረቱ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል።

በመጨረሻም ይህ የ፴፱ኛው የቅዱስ ሲኖዶስ መደበኛ ጉባኤ የተካሄደው የቅዱስ ሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ የሆኑት ታላቁ አባት ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ በሚገኙበት በመካነ ሰላም መድኃኔ ዓለም ካቴድራል በመሆኑ ቅዱስ ሲኖዶስ የተሰማውን ደስታ በመግለጽ ምስጋና ያቀርባል። እግዚአብሔር አምላክ በእድሜ ያከበረልንና አእላፋት የሆኑ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችንና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን ያፈሩልን ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅን ላለፉት ዓመታት ይህን ሕጋዊ ሲኖዶስ በዋና ጸሐፊነት በመምራት ላሳዩን አባታዊ አመራር ቅዱስ ሲኖዶስ በድጋሚ ምስጋና እያቀረበ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው ከሆኑት የአክላንድ መካነ ሰላም መድኃኔዓለም ካቴድራል ምእመናን ጋር በመሆን የሲኖዶሱን መደበኛ ጉባኤ አስደናቂ በሆነ ኦርቶዶክሳዊ ፍቅርና ትህትና ስላስተናገዱልን ብፁዕ አባታችንን የመካነ ሰላም መድኃኔ ዓለም ካቴድራል ካህናት ፣የቦርድ አባላትና ምዕመናንን ታላቅ ምስጋና በማቅረብ ጉባኤው በሰላም ተፈጽሟል።

እግዚአብሔር አምላክ አገራችን ኢትዮጵያንና ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ይባርክ!

አባ መልከጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ

የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ